# የነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎች

በአውራጃው ነፃ የህዝብ ት/ቤት አገልግሎትን ማግኘት የሚችሉት የኮሎምቢያ አውራጃ(ዲሲ) ነዋሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ጠቅላላ በህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች ስለ ነዋሪነታቸው ማለትም በአውራጃው ስለመኖራቸው ማረጋገጫ ማቅረብ አልያም የትምህርት ክፍያ መክፈል አለባቸው፡፡ እነዚህ መመሪያዎች ለትምህርት ቤቱ ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለሌሎች የነዋሪነት ማረጋገጫ ህጉ በግልፅ ተግባራዊ እንዲሆን ለማስቻል የቀረቡ ናቸው፡፡

**ነዋሪነትን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- ለእያንዳንዱ ተማሪዎች ትምህርት ቤቶቹ የተሟላ የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ የሚያስፈልግ ሲሆን ክፍል “ሀ” እና ክፍል “ለ” በትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች ይሞላል፡፡ (ተማሪው በሌላ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ የተመዘገበ ከሆነ) እና ተማሪውን የሚያስመዘግበው ክፍል “ሐ” ይሞላል፡፡ ከዲሲ የመኖሪያ ማረጋገጫ ቅጽ በኋላ ትምህርት ቤቶቹ የደጋፊ ሰነዶቹን ቅፁን ለመሙላት ጥቅም ላይ የዋሉትን የነዋሪነት ማረጋገጫ ሰነድ እና ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ ሰነዶችን መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የተማሪዎች ምዝገባ ምርመራ ጊዜ ትምህርት ቤቶቹ የእነዚህን ሰነዶች እና ቅፆች ኮፒ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡[1]

- ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ኦሪጅናል ሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የት/ቤት ኃላፊዎች የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ቅፁን ከሞሉ በኋላ ኦርጅናል ሰነዶቹን በመገምገም ትክክለኛነታቸውን፣ ሰነዶቹ ላይ ያለው ስም ክፍል "ሐ" ላይ ከተፈረመው ስም ጋር መመሳሰሉን እንዲሁም ሰነዶቹ የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ቅፅ ለመሙላት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ለምሳሌ ቀን እና የሰነድ ዓይነት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

- የእያንዳንዱ ተማሪ የነዋሪነት ሁኔታ በመጀመሪያ በኮሎምቢያ ግዛት የህዝብ ትምህርት ቤት በሚመዘገብበት ጊዜ ጥቅምት 05 (ጥቅምት 05 ቅዳሜ ወይም እሁድ በሚሆንበት ጊዜ በቀጣይ የትምህርት ቀን) ወይም የመጀመሪያው ምዝገባ ከተደረገ በ10 ቀናት ውስጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የተማሪው የነዋሪነት ሁኔታ በየዓመቱ ከዚህ በኋላ በድጋሚ የሚስተካከል ይሆናል፡፡ የዓመታዊ ማረጋገጫው ከሚያዝያ 01 በፊት በእያንዳንዱ ዓመት መሆን የለበትም፡፡ የተማሪው የነዋሪነት ሁኔታ በመስፈርት 1 ወይም 2 ላይ በተገለፁት መሰረት አጥጋቢ በሆኑ ሰነዶች ወይም ተማሪው ቤት አልባ መሆኑን በሚያስረዱ ሰነዶች መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡[2]

**የሌላ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ ሰነዶች**

“ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ” ተብሎ የሚገለፀው ግለሰብ ከወላጆች ወይም በፍርድ ቤት ከተወከለ እንክብካቤ ሰጪ በተለየ ከታዳጊው ጋር አብሮ በመኖር እንክብካቤ እና ድጋፍ የሚሰጥ ግለሰብን ነው፡፡ ይህ ግለሰብ የታዳጊው ወላጆች፣ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ለልጁ እንክብካቤ መስጠት በማይችልበት ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ ወላጅ ወይም በፍርድ ቤት የተወከለ አሳዳጊ ከዚህ በታች በሳጥን ከተመለከቱት ቢያንስ አንዱን ምክንያት የሚያሟላ ከሆነ ለታዳጊው እንክብካቤ ወይም ድጋፍ መስጠት አይችልም ተብሎ ይታሰባል፡፡

| | |
|---|---|
| ☐ ታዳጊውን ትተዋል | ☐ በውትድርና ግዳጅ ላይ ናቸው |
| ☐ ታስረዋል | ☐ ሞተዋል |
| ☐ በጉዳት ወይም ቸልተኝነት አብረው አይኖሩም | ☐ የከፍተኛ ህመም ተጠቂ ናቸው |

በተጨማሪም ወላጅ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ አሳዳጊ እንክብካቤ ወይም ድጋፍ መስጠት የማይችልባቸው ሁኔታዎች በሳጥን ውስጥ ከተገለፁት ውጭ አጥጋቢ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

[1] የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅፅ ከነደጋፊ ሰነዶቹ ፋይሉ ውስጥ ያላካተተ ተማሪ የዲሲ ነዋሪ እንዳልሆነ ተደርጎ ስለሚቆጠር የተፈረመበት የክፍያ እቅድ ግልባጭ ወይም ሙሉ ክፍያ መከፈሉን የሚጠቁም ማስረጃ በኦዲተሩና በኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

[2] በት/ቤቱ የማኪኒ-ቬንቶ ደንብ መሰረት የቤት አልባ ተማሪዎች አስተባባሪ ተገቢው ቅጾች በቤት አልባው ተማሪ የነዋሪነት ፋይል ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ የህፃኑ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ መሆኑን ከዚህ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን በማቅረብ የነዋሪነት ማረጋገጫ ሂደቱ አካል ማድረግ ይቻላል፡፡[3]

1. ከቀድሞ ትምህርት ቤት ልጁን በአሳዳጊው ስር የሚገኝ መሆኑን የሚያሳይ የትምህርት ቤት መዛግብት

   ሀ. ከኤስቲኤአር ዳታ ቤዝ የተወሰደ
   ለ. የተፈረመ የሪፖርት ካርድ (ምስክር ወረቀት)
   ሐ. ሌሎች የትምህርት ቤት መዛግብት

2. ልጁ በአሳዳጊው ስር የሚገኝ መሆኑን የሚያሳይ የክትባት ወይም የሕክምና መዝገብ
3. እንክብካቤ ሰጪው ለልጁ የህዝባዊ ወይም የህክምና ጥቅማጥቅም የሚያገኝበት ማረጋገጫ ከተሰጠበት ቀን 12 ወራት ያላለፈ
   ሀ. ደጋፊ የዓመታዊ ገቢ ጥቅማጥቅም ማስታወሻ ወይም ሰነድ
   ለ. ቲ.ኤ.ኤን.ኤፍ ማረጋገጫ የገቢ ማስታወሻ ወይም የማረጋገጫ ደብዳቤ
4. የተማሪ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ መሆኑን የሚያረጋግጥ የተፈረመ የቃለ መሃላ መግለጫ ደብዳቤ[4]፡፡ መደበኛ ቅፁ ከአካባቢው ትምህርት ቤት ማግኘት ይቻላል፡፡
   ሀ. ዲ.ሲ.ፒ.ኤስ ወይም ቻርተር ትምህርት ቤቶች መግለጫው ትክክለኛ እንዳልሆነ ካሰቡ ተማሪውን የሚመዘግብ ቢሆንም ጉዳዩን ለምርመራ ወደ ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. የሚመሩ ይሆናል፡፡
5. ከህግ አካል፣ ከህክምና ወይም ከማህበራዊ አገልግሎት ባለሙያ[5] ግለሰቡ የታዳጊው እንክብካቤ ሰጪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ 12 ወራት ያላነሰ

**የነዋሪነት ማረጋገጫ መስፈርቶች (1)**

ከዚህ የሚከተሉት አንዱ በኮሎምቢያ አውራጃ(ዲሲ) የነዋሪነት ሁኔታዎችን ያረጋግጣል፡፡

| | የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ተቀባይነት ያላቸው ዝርዝሮች | ሰነዱ የሚከተለውን ማሳየት ይኖርበታል |
|---|---|---|
| 1. | የክፍያ ሰነድ | ሀ. ከተሰጠ በ45 ቀናት ውስጥ መሆን ይኖርበታል፡፡<br>ለ. ልጁን ያስመዘገበው ግለሰብ ስም<br>ሐ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ<br>መ. የዘመኑ የዲሲ የደሞዝ ግብር ተቀናሽ |
| 2. | ከዲሲ መንግስት የተሰጠ የገንዘብ እርዳታ መረጃ ከዚህ በታች በሚከተሉት መልኩ<br>ሀ. ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ የገቢ ማረጋገጫ ወይም የማረጋገጫ ደብዳቤ<br>ለ. የህክምና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት<br>ሐ. ከቤት እና መጠለያ ድጋፍ የቤቱ ባለስልጣን ስልክ እና ስም ወይም ማረጋገጫ ደብዳቤ<br>መ. ከሌሎች የዲሲ መንግስት ፕሮግራሞች የፋይናንስ እገዛ ማረጋገጫ | ሀ. ከተሰጠ በ12 ወራት ቆይታ ውስጥ የሚገኝ<br>ለ. ልጁን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ስም እና<br>ሐ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |

| | | |
|---|---|---|
| 3. | ደጋፊ የዋስትና ገቢ ዓመታዊ ጥቅማጥቅም ማስታወሻ | ሀ. ከተሰጠ በ12 ወራት ቆይታ ውስጥ የሚገኝ<br>ለ. ልጁን ያስመዘገበው ግለሰብ ስም እና<br>ሐ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |
| 4. | በዲሲ የግብር እና ገቢ ባለስልጣን የተረጋገጠ የዲ40 ቅፅ ግልባጭ | ሀ. ልጁን ያስመዘገበው እንክብካቤ ሰጪ ስም<br>ለ. የዲሲ ግብር ለቀድሞ ዘመን የተከፈለበት ማረጋገጫ |

[3]ከ 1-5 ከተዘረዘሩት አንዱን ከማቅረብ በተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪው የነዋሪነት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

[4]በኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. የተሰጠውን የሌላ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ የቃለ መሃላ መግለጫ ቅፅ ይመልከቱ፡፡

[5]በኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. የተሰጠውን የሌላ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ ማረጋገጫ ቅፅ ይመልከቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 5. | የወታደራዊ የቤት ትዕዛዝ | ሀ. የተማሪው ስም እና ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ስም እና<br>ለ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |
| 6. | ታዳጊውን የኮሎምቢያ አውራጃ(ዲሲ) የሚሳድገው መሆኑን የሚያመለክት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መረጃ | ሀ. የተማሪው ስም |
| 7. | የኤምባሲ ደብዳቤ | ሀ. በወቅታዊ የትምህርት ዘመን ከሚያዝያ 01 በኋላ የተሰጠ<br>ለ. ልጁን ያስመዘገበው ግለሰብ ስም<br>ሐ. የጽ/ቤቱ ማህተም እና<br>መ. ተማሪውን ያስመዘገበው ግለሰብ እና ተማሪው በዲሲ የኤምባሲው ንብረት ውስጥ መኖራቸውን የሚያሳይ ማረጋገጫ |

የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ሲባል ከዚህ የሚከተሉት ሰነዶች የኮሎምቢያ ክልልን የግል ገቢ ግብር 1) ደብሊው-2 ቅጽም፣ 2) የፌደራል የገቢ ግብር ተመላሽ ወይም 3) የአውራጃው የገቢ ግብር ተመላሽ (በግብር እና ገቢዎች የዲሲ ጽ/ቤት ካልተረጋገጡ በቀር) እንደማረጋገጫነት መቅረብ **አይኖርባቸውም**፡፡

የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ሲባል የሚከተሉት ከዲሲ መንግስት የተሰጡ የፋይናንስ እገዛ ማረጋገጫ ሰነዶች መቅረብ **አይኖርባቸውም**: 1) የችግረኛ ቤተሰቦች እርዳታ መታወቂያ ደብተር 2) የህክምና መታወቂያ ደብተር 3) ከአውራጃው የተቀጣሪነት መታወቂያ ደብተር (የዲሲ መንግስትን ጨምሮ) ወይም 4) ከዲሲ ነዋሪ የተፃፈ ደብዳቤ

## የነዋሪነት ማረጋገጫ መስፈርቶች (2)

ቀደም ሲል በተቀመጠው ሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩት በማይገኙበት ጊዜ ከዚህ በታች ከተገለፁት ዝርዝሮች ሁለት(2) የሚሆኑት በኮሎምቢያ አውራጃ(ዲሲ) የነዋሪነት ማረጋገጫ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ የቀረበው ዝርዝር ላይ ያለው ስም እና አድራሻ ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

| | የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ተቀባይነት ያላቸው ዝርዝሮች | ሰነዱ የሚከተለውን ማሳየት ይኖርበታል |
|---|---|---|
| 1. | ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ | ሀ. ልጁን ያስመዘገበው ግለሰብ ስም<br>ለ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |
| 2. | ጊዜው ያላለፈበት የኪራይ ውል ስምምነት | ሀ. ልጁን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ስም<br>ለ. ወቅታዊ የዲሲ አድራሻ እና<br>ሐ. ያለፉት 2 ወራት የኪራይ ክፍያን የሚያሳይ የክፍያ ደረሰኝ ወይም የተሰረዘ ቼክ |

| | | |
|---|---|---|
| 3. | ጊዜው ያላለፈበት የአሽከርካሪነተ ፈቃድ ወይም ሌሎች የአሽከርካሪነት ፍቃድ ያልሆኑ መታወቂያዎች | ሀ. ልጁን ያስመዘገበው ግለሰብ እና<br>ለ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |
| 4. | አንድ የአገልግሎት ደረሰኝ (የጋዝ፣ የኤሌክትሪክ እና የውሃ ደረሰኝ ተቀባይነት አላቸው)፡፡ | ሀ. ልጁን ያስመዘገበው እንክብካቤ ሰጪ ስም<br>ለ. ወቅታዊ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻ<br>ሐ. ያለፉት 2 ወራት የአገልግሎት ክፍያን የሚያሳይ የክፍያ ደረሰኝ ወይም የተሰረዘ ቼክ |

የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የሚከተሉት ዝርዝሮች እንደ የዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ ወይም አሽከርካሪ ፈቃድ በሚለው ዘርፍ መቅረብ **አይኖርባቸውም**፡ 1)የተሽከርካሪ ባለቤትነት ወይም 2)የተሽከርካሪ መድን

ወይም ለዲሲ የመኖሪያ ማረጋገጫ ዓላማ ሲባል ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝሮች በአገልግሎት ሰነድነት መቅረብ **አይኖርበትም**፡ 1)የስልክ ደረሰኝ ወይም 2)የኬብል ደረሰኝ

*ትምህርት ቤቱ ከኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. በሌላ መልኩ እስካልተገለፀ ድረስ በምዝገባ ቅፁ ላይ የተመዘገበው ሰነድ ብቻ የመኖሪያነት ማረጋገጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ አሳዳጊው ወይም እንክብካቤ ሰጪው ሌሎች አይነት ሰነዶች ቢያቀርብም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡*